የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት
የኢንቨስትመንትና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ

Central Ethiopia Regional State
Investment & Industry Development
Bureau

ቁጥር [illegible]
Ref.No
ቀን 6/11/2018
Date

ለ..........ዞን ኢንቨ/ኢንዱ/ ልማት መምሪያ

ለ..........ል/ዩ ወረዳ ኢንቨ/ኢንዱ ልማት ጽ/ቤት

<u>ባሉበት፤</u>

ጉዳዩ፡- <u>የኢንቨስትመንት ፈቃድ አሰጣጥ መመሪያን ይመለከታል</u>

የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ኢንቨስትመንትና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ በክልሉ ያለውን የኢንቨስትመንት ፍሰት ቀልጣፋ፣ ግልጽና ተደራሽ ለማድረግ የሚያስችል የኢንቨስትመንት ፈቃድ አሰጣጥ መመሪያ አዘጋጅቷል።

ይህ መመሪያ የተዘጋጀው በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግሥት አስፈፃሚ አካላት ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 199/2015 አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ (ሀ) በተሰጠው ሥልጣንና ኃላፊነት መሠረት ነው።

ስለሆነም የተዘጋጀውን የኢንቨስትመንት ፈቃድ አሰጣጥ መመሪያ ከዚህ ሸኚ ደብዳቤ ጋር .... ገጽ አያይዘን የላክን መሆኑን እየገለጽን፣ መመሪያው በክልሉ ፍትህ ቢሮ ተመዝግቦ ከጸደቀበት ቀን 30/10/2018 ዓ.ም ጀምሮ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን ማስተናገድ የሚቻለው በጸደቀው መመሪያ መሰረት ብቻ እንዲሆን እናሳስባለን።

ከሰላምታ ጋር!

ዶ/ር አባስ መሐመድ አህመ...
የኢንቨስትመንትና ኢንዱስት...
ልማት ቢሮ ኃላ...
Dr. Abas Moham...
Investment & Indu...
Development Bur...

ግልባጭ፡-

- ለቢሮ ኃላፊ
- ለኢንቨ/ዲያስፖራ ዘርፍ ሀላፊ
- ለኢንዱስትሪ ዘርፍ ሀላፊ

<u>በ-ታጅራ፤</u>

Tell:-0461451864/0461451649/0461457566 email:-cerinvestindustry@gmail.com
Website:-https://www.ceriidb.gov.et https://www.facebook.com

የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት ኢንቨስትመንትና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ

ቡታጅራ 3ኛ ዓመት ቁጥር... ሰኔ 2018 ዓ.ም	በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ	Butajira 3rd Year No JULY /2026

መመሪያ ቁጥር 92/2018 ዓ.ም

በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት ኢንቨስትመንትና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ የኢንቨስትመንት ፈቃድ አሰጣጥ መመሪያ

መግቢያ

የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት ወደ ክልሉ በከፍተኛ ሁኔታ እየመጣ ያለውን የኢንቨስትመንት ፍሰት ፍጥነቱን ጠብቆ ማስኬድ ይቻል ዘንድ የቢሮው አገልግሎት አሰጣጥ ወጥና ግልጽ በማድረግ ቀልጣፋና ተጠያቂነት ያለው አሰራር መዘርጋት አስፈላጊ መሆኑ ስለታመነበት፣

የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት ኢንቨስትመንትና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ በክልሉ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 199/2015 አንቀጽ 39(2) በተሰጠው ስልጣንና ተግባር መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል::

ክፍል አንድ

ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት ኢንቨስትመንትና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ የኢንቨስትመንት ፈቃድ አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር 92/2018" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. ትርጓሜ፡-

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1. "የሀገር ውስጥ ባለሀብት" ማለት ኢትዮጵያ ውስጥ ካፒታል ሥራ ላይ ያዋለ ባለሃብት ሆኖ፡-

   ሀ. የኢትዮጵያ ዜጋ የሆነ፣

   ለ. ሙሉ በሙሉ በኢትዮጵያዊ ዜጋ የተያዘ ኢትዮጵያ ውስጥ የተቋቋመ ድርጅት፣
   ሐ. ወደ ኢንቨስትመንት የተሸጋገረ አርሶ አደር ወይም አርብቶ አደር፣
   መ. መንግሥት፣

   ሠ. በኢንቨስትመንት ስራ የሚሳተፍ የመንግስት የልማት ድርጅት፣
   ረ. አግባብነት ባለው ሕግ የተቋቋመ የህብረት ሥራ ማህበር፣
   ሰ. አግባብነት ባለው ሕግ ወይም ኢትዮጵያ ባፀደቀችው ዓለም አቀፍ ስምምነት መሠረት እንደ ሀገር ውስጥ ባለሀብት የተቆጠረ የውጭ ሀገር ዜጋ ወይም ድርጅት፣
   ሸ. በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ ከሀ እስከ ሰ በተመለከቱት በማናቸውም መካከል በጋራ ኢትዮጵያ ውስጥ የተቋቋመ ድርጅት፣

2. "የፈቃድ ለውጥ" ማለት አንድ ድርጅት በትግበራ ወይም በከፊል ማምረት ወይም ሙሉ በሙሉ በማምረት ሂደት ላይ እያለ፣ ፕሮጀክቱ አዋጭነት እንደሌለው ሲታመንና በሌላ ሀገራዊና ክልላዊ ፋይዳ ባለው ፕሮጀክት ቢተካ የተሻለ መሆኑ በድርጅቱ ባለቤትና ፈቃድ በሰጠው አካል ሲታመንበት በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ የሚደረግ የፕሮጀክት

ለውጥ ሆኖ ስም፣ ፕሮጀክት፣ ካፒታልና ስራ አስኪያጅ ተለውጠው የሚሰጡ አገልግሎቶችን ያካትታል፤

3. "የካፒታል ለውጥ" ማለት የኢንቨስትመንት ፈቃድ ለባለሀብቱ ሲሰጥ የተመዘገበው ካፒታል የታቀደውን ፕሮጀክት ለማከናወን ያነሰ እንደሆነ ሲታመን እንዲጨመር በባለሀብቱ የሚቀርብ ጥያቄ ነው፤

4. "የስም ለውጥ" ማለት የባለሀብቱ ወይም የድርጅቱ ስም ለውጥ ሲሆን ይህም በተጀመረ ፕሮጀክት ማህበር በመመስረት ከባለ ይዞታነት ወደ ማህበር በማዛወር ወይም ፕሮጀክቱን ሙሉ በሙሉ በሽያጭ፣ በስጦታ ወይም በውርስ ለሌላ አካል በማስተላለፍ የሚደረግ ለውጥ ነው፤

5. "የአገልግሎት ክፍያ" ማለት አዲስ ፈቃድ ለመስጠት፣ ወይም ለማደስ ወይም የፈቃድ፣ የስምና የካፒታል ለውጥ ለማድረግ የሚከፈል ክፍያ ነው፤

6. "አዲስ የኢንቨስትመንት ፈቃድ" ማለት በተለያዩ ኢንቨስትመንት ዘርፎች የሚሰማራ ባለሀብት የተጠየቀውን የካፒታል መጠን በማሟላት እንዲያለማና መብቱን ተጠቅሞ ስራውን እንዲያከናውን ለማስቻል ሥልጣን በተሠጠው አካል የሚሰጥ ፈቃድ ነው፤

7. "አግባብ ያለው የኢንቨስትመንት መሥሪያ ቤት" ማለት በክልል፣ በዞን እና ልዩ ወረዳ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ለመስጠት ወይም ኢንቨስትመንትን ለማስተዳደር ሥልጣን የተሰጠዉ የሃእርከኑ መስተዳድር አካል ነዉ፤

8. "ቢሮ" ማለት የኢንቨስትመንትና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ ነው፤

9. "ማደስ" ማለት አንድ ባለሀብት ምርቱን ወይም አገልግሎቱን ማቅረብ እስከሚጀምር ጊዜ ድረስ በየዓመቱ ፈቃድ ወደ ሰጠው አካል በመቅረብ ተገቢውን የአገልግሎት ክፍያ ከፍሎ የኢንቨስትመንት ፈቃዱን ማሳደስ ነው፤

10. "ማገድ" ማለት አንድ ባለሀብት የኢንቨስትመንት ፈቃድ ካወጣ በኋላ የኢንቨስትመንት አዋጅ፣ ደንብና መመሪያዎችን በሚጻረር መልኩ ሲንቀሳቀስ የተገኘ እንደሆነ ከ 6 (ስድስት) ወር ላልበለጠ ጊዜ የተሰጠውን ማስተካከያ እስከሚያሻሽል ድረስ ልዩ ልዩ የኢንቨስትመንት ማበረታቻዎች ተጠቃሚ እንዳይሆን ማድረግ ነው፤

11. "መሬት የማያስፈልገው ኢንቨስትመንት" ማለት የመሬት ጥያቄ የማያስፈልገው ኢንቨስትመንት ነው። ይህም ኮንስትራክሽን፣ ማሽነሪ ኪራይ፣ አስጎብኚነትና የመሳሰሉትን የሚያካትት ነው።

12."መስረገዝ" ማለት አንድ በሕግ አግባብ የተሰጠን የኢንቨስትመንት ፈቃድ አንድ ባለሀብት ከኢንቨስትመንት አዋጁ ደንብና መመሪያ በሚጻረር መንገድ ሲጠቀምበት በመገኘቱ፣ ፈቃድ የሰጠው አካል ድርጅቱ በፈቃዱ ያገኘው የነበረ ያለፈውን፣ የአሁኑንና የወደፊቱን ጥቅማ ጥቅም በሕግ አግባብ ማንሳት ነው፣

13."ማስፋፋት ወይም ማሻሻል" ማለት ሊደረስበት የሚችል የነበረ ድርጅትን የማምረቻ ወይም አገልግሎት የመስጠት አቅም ቢያንስ ሃምሳ በመቶ (50%) በመጠን በማሳደግ ወይም የነበረ ድርጅትን አዲስ የማምረቻ ወይም አገልግሎት መስጫ መስመር በመጨመር ምርትን ወይም አገልግሎትን ቢያንስ መቶ በመቶ (100%) በዓይነት ማሳደግ ወይም በሁለቱም ማሳደግን ያጠቃልላል፣

14."ምደባ" ማለት በከተማና በገጠር የሚገኝ መሬትን የላቀ ማኀበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያላቸው የኢንቨስትመንት ሥራዎችን በመመዘን ሥልጣን ባለው አካል በሊዝ መነሻ ወይም በምደባ የሚፈቀድበት አሰራር ነው፣

15."ምትክ ፈቃድ መስጠት" ማለት ፕሮጀክቱ በትግበራ ላይ ባለበት ወቅት የኢንቨስትመንት ፈቃድ ከጠፋ ወይም ከተበላሸ በባለሀብቱ በሚቀርብ የምትክ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ጥያቄ የሚሰጥ ፈቃድ ነው፣

16."የመንግስት የልማት ድርጅት" ማለት በመንግስት ሙሉ ባለቤትነት ሥር የሚገኝና የማምረት፣ የማከፋፈል፣ የመገንባት፣ አገልግሎት የመስጠት ወይም ሌሎች የኢኮኖሚ ተግባራቶችንና ከዚህ ጋር የተያያዙ ሥራዎችን የሚሰራና የኢንቨስትመንት ፈቃድ ያለው ድርጅት ነው፣

17."ካፒታል" ማለት የአገር ውስጥ ወይም የውጭ ገንዘብ፣ የሚተላለፍ ሰነድ፣ የማምረቻ ወይም የአገልግሎት መስጫ መሳሪያ፣ ህንፃ፣ የሥራ ማስኬጃ ካፒታል፣ የንብረት መብት፣ የአዕምሮአዊ ንብረት መብት ወይም ሌላ የሚዳሰስ ወይም የማይዳሰስ የንግድ ሀብት ነው፣

18."ኢንቨስትመንት" ማለት አዲስ ድርጅትን ለማቋቋም፣ ወይም ነባር ድርጅትን ሙሉ ለሙሉ ወይም በከፊል ለመግዛት፣ ለማስፋፋት ወይም ለማሻሻል በባለሀብት በገንዘብ ወይም በዓይነት ወይም በሁለቱም የሚደረግ የካፒታል ወጪ ነው፤

19."ክልል" ማለት የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት ማለት ነው፣

20."ድርጅት" ማለት ለትርፍ የተቋቋመ ድርጅት ነው።

3. የፆታ አገላለጽ

በዚህ መመሪያ ውስጥ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸ አነጋገር ሴትንም ይጨምራል፡፡

4. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ውስጥ በሕግ የኢንቨስትመንት ፈቃድ እንዲሰጡ ስልጣን በተሰጠው በቢሮውና በሁሉም የዞንና የልዩ ወረዳ ኢንቨስትመንት መምሪያዎች /ጽ/ ቤቶች እንዲሁም በክልሉ ውስጥ በኢንቨስትመንት ሥራ ላይ በተሰማሩ ባለሀብቶች ሁሉ ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

ክፍል ሁለት

የኢንቨስትመንት ፈቃድ አስፈላጊነት፣ አሰጣጥና ቅድመ ሁኔታዎች፦

5. የኢንቨስትመንት ፈቃድ አስፈላጊነትና አሰጣጥ

የሚከተሉት ባለሀብቶች የኢንቨስትመንት ፈቃድ ያስፈልጋቸዋል፦

1. በክልል ደረጃ፣ በዞኖች እና በልዩ ወረዳዎች ኢትዮጵያዊ ዜግነት ብቻ ላላቸው ግለሰቦችና ማኅበራት የኢንቨስትመንት ማበረታቻ ባላቸው ዘርፎች ለመሠማራትና የማበረታቻ ተጠቃሚ መሆን ለሚፈልጉ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ይሰጣል፡፡
2. የማስፋፊያ ወይም የማሻሻያ ኢንቨስትመንት ማካሄድ የሚፈልግ ባለሀብት ሆኖ ኢንቨስትመንት ማበረታቻ በሚሰጥበት መስክ ውስጥ የሚወድቅ ከሆነ እና ባለሀብቱ ከማበረታቻ ተጠቃሚ መሆን ከፈለገ፣
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የተደነገገው ቢኖርም ማንኛውም ባለሀብት በማናቸውም ጊዜ የሀገር ውስጥና የውጭ ባለሀብት የኢንቨስትመንት ፈቃዶችን በአንድ ላይ ሊይዝ አይችልም፡፡
4. የኢንቨስትመንት ፈቃድ በመንግሥት በተሰጠ መሬት፣ አስቀድሞ በተያዘ ወይም በግል ይዞታ፣ በኪራይ እንዲሁም የመሬት ጥያቄ በማያስፈልጋቸው ኢንቨስትመንቶች ሊሰጥ ይችላል፡፡

6. የኢንቨስትመንት ፈቃድ ለማውጣት የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎች

1. አዲስ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ለመስጠት

ሀ. የሥራውን ምንነት የሚገልጽ የፕሮጀክት ፕሮፖዛል፤

ለ. የስድስት ወራት እንቅስቃሴ ያለውና ቀሪ ሂሳቡ በፕሮፖዛሉ ከተመዘገበው ጠቅላላ ካፒታል ቢያንስ 30% (ሠላሳ በመቶ) የሆነ የካፒታል አቅም ማሳያ የባንክ ስቴትመንት ከባንኩ ማረጋገጫ ደብዳቤ ጋር፤

ሐ. ወቅታዊ የሆነ የነዋሪነት መታወቂያ ካርድ እና 3 (ሶስት) ጉርድ ፎቶግራፍ፤

መ. ዲያስፖራ ከሆነ ዲያስፖራ መሆኑን እና የፋይናንስ አቅም ስለመኖሩ የሚያሳይ በውጪ ጉዳይ ወይም በዲያስፖራ አገልግሎት መስሪያ ቤት የተረጋገጠ ማስረጃ ማቅረብ፤

ሠ. ማህበር ከሆነ የመመስረቻ ጽሁፍ፤ መተዳደሪያ ደንብ፤ የምዝገባ ሰርተፍኬት እና የግብር መከፈያ መለያ ቁጥር ሰርተፍኬት።

2. ማስፋፊያ ፈቃድ ለመስጠት

ኢንቨስትመንት ማስፋፊያ የሚሰጠው ነባሩ ፕሮጀክት 100% (መቶ በመቶ) አፈፃፀም ደረጃ ላይ ከደረሰ፤ የቀረበው ፕሮጀክት ከነባሩ ፕሮጀክት ጋር ተመጋጋቢ መሆኑና ውጤታማነቱ የተረጋገጠ ሲሆን ብቻ ሲሆን ቀጥሎ የተዘረዘሩት መስፈርቶች መሟላት ይኖርባቸዋል፦

ሀ. የማስፋፊያ የፕሮጀክት ፕሮፖዛል እና የተጨማሪው ካፒታል የባንክ ስቴትመንት፤

ለ. ከሚመለከተው አካል የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ፤

ሐ. የነባር ድርጅቱ የፀና የንግድ ሥራ ፈቃድ ፎቶ ኮፒ፤

መ. የግብር መከፈያ መለያ ቁጥር ወይም የምስክር ወረቀት /ሰርተፍኬት/፤

ሠ. በቀድሞው ፕሮጀክት ያለውን አፈጻጸም የሚያሳይ የድጋፍ ደብዳቤ፤

ረ. ጉዳዩ በቀጥታ ከሚመለከተው የመንግስት አካል ወይም እውቅና ባለው ባለሙያ የተዘጋጀ ወቅታዊ የኦዲት ሪፖርት።

3. ከመሬት ጋር የተያያዘ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ሲወጣ መሟላት ያለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች፡-

    1. ከመንግስት በሚሰጥ መሬት ኢንቨስት የሚደረግ ከሆነ የክልሉ መንግስት በካቢኔ መሬቱ ለባለሀብቱ እንዲተላለፍ የወሰነበት ደብዳቤ፣ መሬቱ የከተማ ከሆነ የይዞታ ማረጋገጫ እና የሊዝ ውል፣ እንዲሁም መሬቱ የገጠር ከሆነ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ እና x-y ኮርዲኔት ያለው መሆን ይኖርበታል። በተጨማሪም በሚመለከተው የፍትህ ተቋም በኩል በውል ሰጪ እና በውል ተቀባይ መካከል የተፈጸመ የውል ሰነድ መቅረብ ይገባል፣
    2. በግል ይዞታ ከሆነ የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ እና የከተማ መሬት ከሆነ ለፕሮጀክቱ የታሰበው መሬት ለፕሮጀክቱ አግባብነት ያለው ስለመሆኑ በይዞታ ማረጋገጫው ላይ የተገለጸ ሰነድ፣
    3. በኪራይ መሬት ኢንቨስት የሚደረግ ከሆነ በሚመለከተው አካል የፀደቀና ቢያንስ የአሥር ዓመት የኪራይ ውል፣
    4. ማህበር ከሆነ የመመስረቻ ጽሁፍ፣ መተዳደሪያ ደንብ፣ የምዝገባ ሰርተፍኬትና የግብር መክፈያ መለያ ቁጥር ወይም ሰርተፍኬት።

4. መሬት ለማያስፈልጋቸው የኢንቨስትመንት ፈቃድ ሲወጣ መሟላት ያለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች፡-

    1. የኢንቨስትመንት ፈቃድ መጠየቂያ ማመልከቻ በባለሀብቱ /በሕጋዊ ተወካይ የተፈረመ፣
    2. የታደሰ ቀበሌ መታወቂያ፣ የነዋሪነት ማረጋገጫ ወይም ፓስፖርት ኮፒ ከፎቶ ግራፍ ጋር፣
    3. የኢንቨስትመንት ፕሮጀክት ፕሮፖዛል፣
    4. የስድስት ወራት እንቅስቃሴ ያለውና ቀሪ ሂሳቡ በፕሮፖዛሉ ከተመዘገበው ጠቅላላ ካፒታል ቢያንስ 30% (ሠላሳ በመቶ) የሆነ የካፒታል አቅም ማሳያ የባንክ ስቴትመንት ከባንኩ ማረጋገጫ ደብዳቤ ጋር፣
    5. ለማህበር ከሆነና ማህበሩ ከተመሰረተ ስድስት ወር ካልሞላው ወይም የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ከሌለው የፕሮጀክቱ 30% (ሠላሳ በመቶ) በአካውንት መኖሩን የሚገልጽ የባንክ ደብዳቤ፣

6. የባንክ ማስረጃው ከውጭ አገር የሚቀርብ ከሆነ ስለባንኩ ትክክለኛነት በዚያ አገር የውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት፣ ወይም በዚያ አገር ያለው የኢትዮጵያ ኤምባሲ /ቆንጽላ ጽ/ቤት፣ ወይም በአገራችን የሚገኘው የዚያ አገር ኤምባሲ የሰጡበት ማረጋገጫ፣

7. ባለሀብቱ በውጭ አገር ነዋሪ ሆኖ የካፒታል አቅሙን በአገር ውስጥ የሚያሳይ ከሆነ ወቅታዊ የሆነ ፓስፖርትና በባንክ 30% (ሠላሳ በመቶ) ያለው ስለመሆኑ ማረጋገጫ፣

8. ለሥራው የሚያስፈልጉ እቃዎች ወይም ማሽነሪ ተገዝቶ ከሆነ የግዢውን ሰነድ በማቅረብ የባንክ መረጃውን የሚተካ ከአጠቃላይ ካፒታሉ 30% (ሠላሳ በመቶ) ያላነሰ በአይነት ማቅረብ፣

9. የኢንቨስትመንት ፈቃድ በተወካይ የሚጠየቅ ከሆነ ሥልጣን በተሰጠው አካል የተረጋገጠ የውክልና ደብዳቤ ማቅረብ፡፡

5. የቡና መፈልፈያ ኢንዱስትሪ ለማቋቋም፣ የግንባታ ካርታ ለማፅደቅና ዝውውር ለማድረግ መሟላት ያለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች፡-

1. የቡና መፈልፈያ ኢንዱስትሪ ለማቋቋም

ሀ. ለአዲስ ፈቃድ የተጠየቁ መስፈርቶች እንደተጠበቀ ሆኖ በተጨማሪ፡-

ለ. ከዞን፣ ከልዩ ወረዳ ወይም ወረዳ ግብርናና ገጠር ልማት፣ ከአካባቢ ጥበቃ፣ ከጤና፣ ከውኃ፣ ከማዕድንና መስኖ፣ ከመሳሰሉት ተቋማት የተሰጠ የድጋፍ ደብዳቤ እና የጥናት ሰነዶችን ማቅረብ፡፡

2. የእሸት ቡና መፈልፈያ የግንባታ ካርታ ለማጸደቅ፡-

ሀ. የኢንቨስትመንት ሰርተፍኬት፣

ለ. ፕሮጀክቱ ሲፈቀድ የተካሄዱ የጥናት ሰነዶች ከቡናና ቅመማ ቅመም ልማት ኤጀንሲ ማቅረብ፣

ሐ. በስታንዳርድ የተሰራ የፕላን ብሉፕሪንት በ 2 (ሁለት) ኮፒ ማሰራት፡፡

3. የእሸት ቡና መፈልፈያ ኢንዱስትሪ ዝውውር ለማድረግ

ሀ. በሽያጭ፣ በውርስ፣ በስጦታ ዝውውር የተደረገበት የጸደቀ ማስረጃ፣

ለ. በቀደመው ባለሀብት /ድርጅት/ ስም ተሰርቶ የጸደቀው ብሉፕሪንት፣

ሐ. በመቋቋም ላይ የነበረ ፕሮጀክት ከሆነ በተላወረለት ባለሀብት ስም የተሰጠ /የተሰጠ/ የኢንቨስትመንት ሰርተፍኬት፣

መ. ማምረት /አገልግሎት መስጠት/ ከጀመረ የንግድ ሥራ ፈቃድ በአዲሱ ባለሀብት ስም የተመዘገበ፣

ሠ. የፕላኑን ብሉፕሪንት በ 2 (ሁለት) ኮፒ አሰርቶ ማቅረብ፡፡

6. ማዕድን ነክ ውጤቶችን በግብዓትነት ወይም በጥሬ ዕቃነት በመጠቀም የማምረት /አገልግሎት/ ለመስጠት ጥያቄ የሚያቀርቡ ባለሀብቶች፡-

አዲስ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ለማውጣት የተቀመጡ መስፈርቶች እንደተጠበቀ ሆኖ ከክልል ወይም ከዞን ማዕድንና ኢነርጂ መሥሪያ ቤት ፈቃድና የድጋፍ ደብዳቤ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

7. የኢንቨስትመንት ፈቃድ የሚጠይቁ አካላት እና የሚሟሉ ተጨማሪ ቅድመ ሁኔታዎች፡-

   1. ኢንቨስትመንቱ በግለሰብ የሚካሄድ ከሆነ

      ለአዲስ ፈቃድ የተጠየቁ መስፈርቶች እንደተጠበቀ ሆነው፡-

      ሀ. የመታወቂያ ካርድ ፎቶ ኮፒ ወይም የሀገር ውስጥ ባለሀብትነት ሰርተፍኬት ፎቶ ኮፒ፣

      ለ. 3 (ሦስት) የቅርብ ጊዜ ጉርድ ፎቶግራፎች፣

   2. የንግድ ማህበር በሚሆንበት ጊዜ

      ለአዲስ ፈቃድ የተጠየቁ መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆነው፡-

      ሀ. የማህበሩ መመስረቻ ጽሑፍና የመተዳደሪያ ደንብ ፎቶኮፒ፣

      ለ. የንግድ ምዝገባ ሰርተፍኬት፣

      ሐ. የግብር መክፈያ መለያ ቁጥር ወይም ሰርተፍኬት፣

      መ. የንግድ ማህበሩ ስራ አስኪያጅ መታወቂያና የቅርብ ጊዜ 3 (ሦስት) ጉርድ ፎቶግራፍ፣

   3. የመንግስት የልማት ድርጅት በሚሆንበት ጊዜ፡-

      ለአዲስ ፈቃድ የተጠየቁ መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆኖ፡-

      ሀ. የልማት ድርጅቱ የተቋቋመበት ደንብ ፎቶ ኮፒ ወይም የመመስረቻ ጽሁፍና የመተዳደሪያ ደንብ፣

ለ. የድርጅቱ ወቅታዊ ስራ አስኪያጅ ወይም ድርጅቱን ካቋቋመው አካል የተሰጠ ማስረጃና የመታወቂያ ፎቶ ኮፒ፡፡

4. የህብረት ሥራ ማህበር በሚሆንበት ጊዜ

ለአዲስ ፈቃድ የተጠየቁ መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆኖ፡-

ሀ. የማህበሩ መተዳደሪያ ወይም መመስረቻ ደንብ የጸደቀ ፎቶ ኮፒ፣

ለ. የድጋፍ ደብዳቤ ከአደራጁ መሥሪያ ቤት፡፡

8. በኢንዱስትሪ ፓርክ ልማት ኮርፖሬሽን በሚገነቡ ሼዶች ለሚገቡ ባለሀብቶች የሚሰጥ ፈቃድ፡-

ለአዲስ ፈቃድ የተጠየቁ መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆነው፡-

ሀ. ከኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን የድጋፍ ደብዳቤ፣

ለ. ከኮርፖሬሽኑ ጋር የኪራይ ውል የተገባበት ሕጋዊ ሰነድ መቅረብ ይኖርበታል፡፡

9. ባለ ኮከብ ሆቴል ደረጃ ፈቃድ ለመስጠት መሟላት ያለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች፡- የባለ ኮከብ ሆቴል ደረጃ ያሏቸው ሆቴሎች፣ ሎጆች፣ ሪዞርቶችና ሞቴሎች የኢንቨስትመንት ፈቃድ የሚሰጠው ከዚህ ቀጥሎ የተዘረዘሩት መሠረታዊ ነጥቦች ሲሟሉ ነዉ፡-

ሀ. ድርጅቱ መሬት በምደባ የተሰጠው ከሆነ የክልሉ መንግስት በካቢኔ መሬቱ እንዲተላለፍ የወሰነበት ደብዳቤ፣

ለ. የድርጅቱ ይዞታ በግል ከሆነ ለፕሮጀክቱ የታሰበው መሬት ለፕሮጀክት አግባብነት ያለው ስለመሆኑ በይዞታ ማረጋገጫው ላይ የተገለጸ ሰነድ ማቅረብ፣

ሐ. በኪራይ መሬት ኢንቨስት የሚያደርግ ከሆነ በውልና ማስረጃ የጸደቀ ቢያንስ የአሥር ዓመት የኪራይ ውልና ለፕሮጀክቱ የታሰበው መሬት ለፕሮጀክቱ አግባብነት ያለው ስለመሆኑ በይዞታ ማረጋገጫው ላይ የተገለጸ ሰነድ መቅረብ ይኖርበታል፡፡

10. በግብርና፣ አገልግሎት እና ኢንዱስትሪ ዘርፍ የተሠማሩ የግል ባለሀብቶች ኢንቨስትመንት ማስፋፊያ ፈቃድ ለመስጠት፡-

ሀ. አስቀድመው በወሰዱት የኢንቨስትመንት ፈቃድ የተፈቀደው ፕሮጀክት ሙሉ በሙሉ መጠናቀቅና ምርት ወይም አገልግሎት መስጠት መጀመር አለበት፡፡

13. የኢንቨስትመንት ፈቃድ ለማደስ መሟላት ያለባቸው ዝርዝር ቅድመ ሁኔታዎች፡-

ከላይ በአንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ 2 እና 3 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ለማሳደስ፡-

ሀ. ዋናው የኢንቨስትመንት ፈቃድ ሰርተፍኬት፣
ለ. ጥያቄው የቀረበው በወኪል ከሆነ የውክልና ማስረጃ፣
ሐ. የእድሳት ወቅቱ ያለፈበት ከሆነ ፕሮጀክቱ ምርትና አገልግሎት መስጠት ለምን እንዳልጀመረና ወደፊት ሊተገበር ስለሚቻልበት ሁኔታ ከሚመለከተው አካል ማስረጃ ማቅረብ አለበት።

14. በትግበራ ላይ የሚገኝ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክት ስለማስተላለፍ

የንግድ ሥራ ፈቃድ ከማውጣቱ በፊት በሆነና በልዩ ወረዳ ውስጥ በትግበራ ላይ የሚገኝ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቱን ለሌላ ባለሀብት ማስተላለፍ የሚፈልግ ከግብርና ዘርፍ ውጪ የሆነ ማንኛውም ባለሀብት ጥያቄውን በአካባቢው ለሚገኝ የኢንቨስትመንት መሥሪያ ቤት በማቅረብ ሲፈቀድለት ፕሮጀክቱን ማስተላለፍ ይችላል። ሆኖም ግን የሚተላለፈው ፕሮጀክት ቢያንስ 50% (ሃምሳ በመቶ) የለማ መሆን ይኖርበታል።

15. የኢንቨስትመንት ፈቃድን ስለማገድ

1. ማንኛውም ባለሀብት የኢንቨስትመንት አዋጁ ወይም አዋጁን ለማስፈጸም የወጡ ደንቦችንና መመሪያዎችን የጣሰ እንደሆነ አስፈላጊውን የማስተካከያ እርምጃ እስኪወስድ ድረስ አግባብ ያለው የኢንቨስትመንት መስሪያ ቤት የኢንቨስትመንት ፈቃዱን ሊያግድበት ይችላል፤
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የኢንቨስትመንት ፈቃድ በሚከተሉት ሁኔታዎች ሊታገድ ይችላል፡-

   ሀ. አግባብ ላለው የኢንቨስትመንት መሥሪያ ቤት የሚጠየቀውን መረጃ ወይም የፕሮጀክት አፈፃፀም ሪፖርት በትክክል እና በወቅቱ ካላቀረበ ወይም ያላቀረበው ሆን ብሎ ወይም በቸልተኝነት ከሆነ፤

ሰ. የኢንቨስትመንት ፈቃዱን ወይም ዕድሳቱን ያገኘው በማታለል ከሆነ ወይም በሐሰት መረጃ ወይም መግለጫ በማቅረብ ከሆነ፤

ሐ. ያለበቂ ምክንያት የኢንቨስትመንት ፈቃዱን አግባብ ባለው ጊዜ ውስጥ ካላሳደሰ፤

መ. የፕሮጀክት ትግበራ ጀምሮ ፕሮጀክቱን ለማጠናቀቅ ውል በገባው ጊዜ ውስጥ ያለበቂ ምክንያት ካላጠናቀቀ፤

ሠ. በሕጉ መሠረት የተሰጡትን ማበረታቻዎች ከታቀደላቸው ዓላማ ውጭ ካዋለ ወይም ማበረታቻዎቹ ከሕግ ውጭ ለሌላ ሰው ተላልፈው ከተገኙ፤

ረ. ቢሮውን ለማቋቋም የወጣ ማንኛውም አዋጅ፣ ደንብ፣ መመሪያና ድንጋጌዎች እንዲሁም ሌሎች አግባብነት ያላቸው ሕጎች ከተላለፈ፤

ሰ. ለኢንቨስትመንት ሥራ በተረከበው መሬት ላይ የፋይናንስና የዕውቀት ድጋፍ ለማሰባሰብ በማሰብ መሬቱን ለኢንቨስትመንት ትግባር የፈቀደው አካል እውቅናና የድጋፍ ደብዳቤ ውጪ አዲስ ማህበርም ይሁን ተጨማሪ አባላትን በነባሩ ማህበር ካካተተ፤

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የኢንቨስትመንት ፈቃድ የታገደበት ባለሀብት ለዕገዳው ምክንያት የሆነውን ነገር እንዲያስተካክል የ 6 (ስድስት) ወር የጊዜ ገደብ ይሰጠዋል፡፡

16. የኢንቨስትመንት ፈቃድ ስለመሰረዝ፦

የኢንቨስትመንት ፈቃድ የሚሰረዘው በሚከተሉት ሁኔታዎች ነው፦

1. ማንኛውም ባለሀብት የኢንቨስትመንት ፈቃድ ከወሰደበት ጊዜ ጀምሮ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቱን ትግበራ ያለ በቂ ምክንያት ሳይጀምር 2 (ሁለት) ዓመት ካለፈው፤
2. የኢንቨስትመንት ፕሮጀክት ትግበራውን ለማጠናቀቅ አግባብ ካለው የኢንቨስትመንት መሥሪያ ቤት ጋር ከተስማማበት ጊዜ በ 2 (ሁለት) ዓመት ከዘገየ፣ ደረጃ በደረጃ የመጀመሪያ እና ሁለተኛ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ እንዲሰጠው ተደርጎ ማሻሻል ካልቻለ፤
3. በኢንቨስትመንት ውል በተደነገገው የጊዜ ገደብ ውስጥ የኢንቨስትመንት ትግበራ ካልጀመረ፤

4. ለኢንቨስትመንት ፈቃድ መታገድ እንደምክንያት የሆነውን ጉዳይ እንዲያስተካክል በፅሑፍ በተሰጠው ጊዜ ውስጥ ካላስተካከለ፤

5. የኢንቨስትመንት ሥራውን በፈቃዱ ከተወ፤

6. ተፈፃሚነት ባለው ሕግ መሠረት የተሰጡትን ማበረታቻዎች ከታቀደላቸው ዓላማ ውጭ ካዋለ ወይም ከሕግ ውጭ ለሌላ ካስተላለፈ፤

7. በክልል መስተዳድር ምክር ቤት በምደባ መገኘት ያለበትን መሬት ከክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት እውቅናና ይሁንታ ውጪ በተገኘ መሬት የወጣ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ከሆነ፤

8. የኢንቨስትመንት ፈቃድ የተሠረዘበት ባለሀብት ወዲያውኑ ማንኛውንም ማበረታቻ አያገኝም፤

9. በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ 1-6 የተደነገገው ቢኖርም የኢንቨስትመንት መሬት እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን የተሰጠው አካል በሕግ አግባብ የመሬት ውሉን ከሰረዘበት በማንኛውም ጊዜ የኢንቨስትመንት ፈቃድ አብሮ ይሰረዛል፤

10. ፈቃዱን የሠረዘው አካል ለባለሀብቱ እና ለሚመለከታቸው አካላት ፈቃዱ ከተሰረዘበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር በ 10 (አስር) ቀናት ውስጥ ከነሙሉ ማብራሪያው ማሳወቅ አለበት።

11. የኢንቨስትመንት ፈቃድ የተሠረዘበት ባለሀብት ፈቃድ ከተሠረዘበት ቀን ጀምሮ ሲያገኝ የነበረው ጥቅማ ጥቅም ወዲያው ይቋረጣል።

12. የኢንቨስትመንት ፈቃድ ከሰጠው አግባብ ካለው የኢንቨስትመንት መሥሪያ ቤት ውጭ በሌላ ማንኛውም አካል ሊሠረዝ አይችልም።

17. ለኢንቨስትመንት ፈቃድ ዝውውር፣ ለውጥ፣ ምትክና ስረዛ ጥያቄዎች መሟላት ያለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች:-

1. የስም ዝውውር ከግለሰብ ወደ ማህበር ለማድረግ የሚከተሉት ቅድመ ሁኔታዎች መሟላት አለባቸው፡-

ሀ. መሬት ከሰጠው አካል የተሰጠ የድጋፍ ደብዳቤ፣

ለ. የማህበሩ አባላት የተስማሙበትና የጸደቀ ቃለ-ጉባኤ፣

ሐ. ማሻሻያው ወይም የለውጡ መመስረቻ ጽሁፍና መተዳደሪያ ደንብ የጸደቀ፣

መ. ዋና የንግድ ምዝገባ ምስክር ወረቀት፣

ሠ. ፕሮጀክቱ አገልግሎት መስጠት የጀመረ ከሆነ ተቀይሮ የተሰጠበት የንግድ ፈቃድ፣

ረ. የግብር መክፈያ መለያ ቁጥር ወይም ሰርተፍኬት፣

ሰ. የቀደመው ባለሀብት ከገቢ ግብር እና ከተለያዩ ዕዳዎች ነጻ ስለመሆኑ ከሚመለከተው አካል ማረጋገጫ፣

ሸ. የቀድሞው ኢንቨስትመንት ፈቃድ ምስክር ወረቀት፣

ቀ. ጥያቄው በወኪል የቀረበ ከሆነ ሕጋዊ የውክልና ማረጋገጫ፣

በ. የከተማ ኢንቨስትመንት ከሆነ ፕሮጀክቱ በግንባታ ላይ ያለ ስለመሆኑና የዘመኑን የቦታ ኪራይ የከፈለበት ማረጋገጫ፣

ተ. የገጠር ኢንቨስትመንት ከሆነ በውሉ መሠረት ወደ ልማት የገባ ስለመሆኑና የዘመኑን የመሬት ኪራይ ግብር የከፈለበት ማረጋገጫ መቅረብ አለበት።

2. በሽያጭ ወይም በስጦታ ዝውውር ለማድረግ መሟላት ያለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች፦

ሀ. በውልና ማስረጃ የጸደቀ የሽያጭ ወይም የስጦታ ስምምነት ማስረጃ፣

ለ. ዋና የምዝገባ ምስክር ወረቀት፣

ሐ. የግብር መክፈያ መለያ ቁጥር ወይም ሰርተፍኬት፣

መ. የቀድሞው የኢንቨስትመንት ሰርተፍኬት፣

ሠ. የተቀየረበት የንግድ ፈቃድ፣

ረ. የገዢ ወይም የስጦታ ተቀባይ የቅርብ ጊዜ 3 (ሦስት) ጉርድ ፎቶግራፍ፣

ሰ. የግብርና ፕሮጀክት ከሆነ ፕሮጀክቱ 50% (ሃምሳ በመቶ) የለማ ስለመሆኑ ማስረጃ፣

ሸ. በፈቃዱ ስም ብድር የወሰደ ከሆነ የአበዳሪው ክፍል አስተያየት፣

ቀ. በወኪል የቀረበ ከሆነ በውልና ማስረጃ የተሰጠ የውክልና ማረጋገጫ።

3. በውርስ ምክንያት ስም ዝውውር ለማድረግ መሟላት ያለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች፦

ሀ. የማመልከቻ ቅጽ መሙላት፣

ለ. በፍርድ ቤት የጸደቀ የወራሽነት ማረጋገጫ፣

ሐ. ወራሾች ከአንድ በላይ ከሆኑና በአንደኛው ስም የኢንቨስትመንት ፈቃድ እንዲወጣ ከፈለጉ ሥልጣን ባለው አካል የጸደቀ የውል ስምምነት፣

መ. የወራሽ የቅርብ ጊዜ 3 (ሦስት) ጉርድ ፎቶ ግራፍ፣

ሠ. የኢንቨስትመንት ፈቃድ ወይም ሰርተፍኬት፣

ረ. የተቀየረበት ወይም የተመዘገበበት የንግድ ፈቃድ፣

ሰ. የዋና ንግድ ፈቃድ ምዝገባ ምስክር ወረቀት፤

ሸ. የግብር መከፈያ መለያ ቁጥር ወይም ሰርተፍኬት፤

ቀ. በወኪል የቀረበ ከሆነ የውክልና ማረጋገጫ፤

4. የጠፋ ወይም የተበላሸ ሰርተፍኬት ምትክ እንደገና ለማግኘት መሟላት ያለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች፡-

   ሀ. ማመልከቻና የተበላሸውን ሰርተፍኬት፤

   ለ. በወኪል የቀረበ ከሆን የውክልና ማረጋገጫ፤

   ሐ. ለጠፋው ሰርተፍኬት ከፖሊስ የተሰጠ ማስረጃ፤

5. በባለሀብቱ ለሚቀርብ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ስረዛ ጥያቄ መሟላት ያለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች፡-

   ሀ. ለመሰረዝ ያስፈለገበትን ምክንያት የሚገልጽ ማመልከቻ፤

   ለ. የፕሮጀክቱ የልማት እንቅስቃሴ በተመለከተ ከሚገኝበት ዞን ወይም ልዩ ወረዳ የተሰጠ የድጋፍ ደብዳቤ፤

   ሐ. የኢንቨስትመንት ፈቃድ ምስክር ወረቀት፤

   መ. በኢንቨስትመንት ፈቃድ የተገኙ ጥቅሞችና የተገቡ ግዴታዎችን በደንቡ መሠረት የተወጣ ስለመሆኑ ማረጋገጫ፤

   ሠ. በባለሀብቱ ፍላጎት የተሰረዘ ፈቃድ መሰረዙ ከመረጋገጡ በፊት መሬቱ ወደ መሬት ባንክ መመለሱ፣ ማበረታቻ ተጠቃሚ መሆን አለመሆኑ እና ከባንክ ዕዳ ነጻ መሆኑ ማረጋገጫ መቅረብ አለበት፡፡

6. የፕሮጀክት ለውጥ ለማድረግ መሟላት ያለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች፡-

   ሀ. ፕሮጀክት እንዲለውጥ መሬቱን ከሰጠው አካል በምን ፕሮጀክት መተካት እንዳለበት የሚገልጽ የስምምነት ደብዳቤ፤

   ለ. ለውጡን ማድረግ ያስፈለገበትን ምክንያት የሚገልጽ የጽሁፍ ማመልከቻ፤

   ሐ. የአዲሱን ፕሮጀክት ምንነት የሚገልጽ ፕሮፖዛል፤

   መ. የቀድሞው የኢንቨስትመንት ሰርተፍኬትና 3 (ሶስት) ጉርድ ፎቶግራፍ፤

7. የካፒታል ለውጥ ለማድረግ መሟላት ያለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች፡-

   የፕሮጀክት ለውጥ ማድረግ የፈለገ እንድ ባለሃብት ለውጥ ለማድረግ የፈለገበትን ምክንያት በመግለጽ ለዞኑ/ልዩ ወረዳው ኢንቨስትመንትና ኢንዱስትሪ ልማት መምሪያ

/ጽ/ቤት በጽሁፍ አቅርቦ አሳማኝ ሆኖ ከተገኘ መ/ቤቱ ለዞኑ /ልዩ ወረዳ ካቢኔ በማቅረብ ማስወሰን ይኖርበታል። በተጨማሪም ለመጀመሪያው ፕሮጀክት የተፈቀደው የመሬት መጠን ለውጥ እንዲደረግበት ከቀረበው ፕሮጀክት ጋር የሚጣጣም ሆኖ ካልተገኘ በስታንዳርዱ መሰረት በጥንቃቄ ታይቶ የሚወሰን ይሆናል። በስታንዳርዱ ከተቀመጠው የመሬት መጠን በላይ በለውጡ ሊፈቀድ አይችልም። ዞኖችና ልዩ ወረዳዎች የዚህን ውሳኔ ለክልሉ ኢንቨስትመንትና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ በማለባጭ የማሳወቅ ግዴታ አለባቸው።

ሀ. የካፒታል ለውጥ ያስፈለገበትን ምክንያት የሚገልጽ የጽሁፍ ማመልከቻ፣

ለ. በተጨማሪው ካፒታል የሚሰሩ ስራዎችን ምንነት የሚገልጽ አዲስ ፕሮፖዛል፣

ሐ. ለተጨማሪ ካፒታል 30% (ሠላሳ በመቶ) የሚያሳይ የባንክ ስቴትመንት፣

መ. የቀደመው የኢንቨስትመንት ሰርተፍኬትና 3 (ሦስት) ጉርድ ፎቶግራፍ፣

ክፍል አራት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

18. ሪፖርት የማድረግና የመተግበር ግዴታ

የኢንቨስትመንት ፈቃድ ያወጣ ማንኛውም የግል ባለሀብት፤

1. ስለ ኢንቨስትመንቱ አፈፃፀም ሂደት በየ 6 (ስድስት) ወሩ አግባብ ላለው የኢንቨስትመንት መሥሪያ ቤት ሪፖርት ማቅረብ አለበት።
2. አግባብ ባለው የኢንቨስትመንት መስሪያ ቤት መረጃ ሲጠየቅ የመስጠት ግዴታ አለበት።
3. አገልግሎት ሰጪ መሥሪያ ቤቱ ለውይይት፣ ለግብረ-መልስና ለመሳሰሉ ጉዳዮች በሚጠራበት ወቅት የመቅረብ ግዴታ አለበት።
4. የኢንቨስትመንት ፈቃዱን መሠረት አድርጎ ያገኛቸውን ማበረታቻዎች አገልግሎት መረጃ ማስመዝገብና አፈፃፀም ሪፖርት ማድረግ አለበት።

19. የኢንቨስትመንት ፈቃድ የተሠረዘበት የግል ባለሀብት ልዩ ልዩ ማበረታቻን ስለማንሳት፦

የልዩ ልዩ ማበረታቻ መብትን ማንሳትን በተመለከተ፦

1. በከተማም ይሁን በገጠር በየትኛውም የኢንቨስትመንት ዘርፍ ተሰማርቶ የማንኛውም የኢንቨስትመንት ማበረታቻ መብት ተጠቃሚ የሆነ የግል ባለሀብት የኢንቨስትመንት ፈቃድ ከተሰረዘ ኢንቨስትመንትን ለማበረታታት የተፈቀደለትን ማንኛውም የማበረታቻ መብቱ የተነሳ መሆኑ ተገልፆ ጉዳዩ በቀጥታ ለሚመለከታቸው የመንግስት አካላት በ 1 (አንድ) ወር ጊዜ ውስጥ በአድራሻና በግልባጭ እንዲያውቁት ይደረጋል፡፡
2. ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋትና ለማበረታታት በክልሉ የመስተዳድር ምክር ቤት የከተማ መሬት በምደባ እንዲሰጠው የተደረገ ባለሀብት በቂ ክትትልና ድጋፍ ተደርጎለት የአፈፃፀም መሻሻል ባለማሳየቱ ወይም የኢንቨስትመንትን ደንብና መመሪያ በሚጻረር መልኩ ሲንቀሳቀስ በመገኘቱ ምክንያት የኢንቨስትመንት ፈቃድ የተሰረዘበት ባለሀብት መሬት በምደባ ያገኘበትን መብት መነሳቱ ተገልጾ ጉዳዩ በቀጥታ ለሚመለከተው የመንግስት አካል ይላካል፡፡ ጉዳዩ የተገለጸለት አካልም የሕግ አግባብ ተከትሎ እርምጃ በለመወሰዱ ክትትል ያደርጋል፡፡
3. በገጠር ለኢንቨስትመንት ሥራ በምደባ የተሳሰፈ መሬት ጉዳዩ በቀጥታ ከሚመለከተው ፈቃድ ከሰጠው አካል እውቅና ውጭ ሲንቀሳቀስ ወይም ማንኛውም የኢንቨስትመንት ሕግና መመሪያ በሚጻረር መልኩ ሲንቀሳቀስ በመገኘቱ ፈቃድ የተሰረዘበት የግል ባለሀብት በምደባ ያገኘውን የገጠር መሬት ውል ተሰርዞ ወደ መሬት ባንክ እንዲገባ ይደረጋል፡፡

20. የአገልግሎት ክፍያ አከፋፈል በተመለከተ፡-

በዞንና ልዩ ወረዳ ኢንቨስትመንትና ኢንዱስትሪ ልማት መዋቅሮች ለሚሰጡ ፈቃዶች በዚህ መመሪያ አንቀጽ ሥር የተዘረዘሩት የአገልግሎቶች ክፍያዎች ኢንቨስትመንቱ በሚገኝበት ዞን ወይም ልዩ ወረዳ የገቢዎች መስሪያ ቤት ቀርቦ የአገልግሎት ክፍያ ፈጽሞ ፈቃድ ለሚሰጠው አካል የአገልግሎት ክፍያ የተፈጸመበትን ደረሰኝ ሁለተኛውን ኮፒ ማቅረብ ያለበት ሲሆን ፈቃድ የሚሰጠውም አካል ደረሰኙን ከግል ባለሀብቱ ፋይል ጋር አያይዞ ማሰር አለበት፡፡ የአገልግሎት ክፍያዎቹም፡-

የአገልግሎት ዓይነት	ክፍያ በብር
ሀ. አዲስ የኢንቨስትመንት ፈቃድ	5000.00

ለ. የቡና ካርታ ለማፀደቅ	5000.00
ሐ. ፈቃድ ለማደስ	1500.00
መ. ማስፋፊያ	2000.00
ሠ. የፈቃድ ለውጥ	2000.00
ረ. ምትክ ፈቃድ	2000.00

21. ፈቃድ የሚሰጡ አካላትን በተመለከተ፡-

1. ይህ መመሪያ ሥራ ላይ ከዋለበት ቀን ጀምሮ ቀደም ሲል በክልል ደረጃ ይሰጡ የነበሩ ውስን ፈቃዶችን ጨምሮ፣ ልዩ ወረዳዎችን በመጠከል በክልል ደረጃ ይሰጡ የነበሩ ፈቃዶች በዞንና ልዩ ወረዳ ኢንቨስትመንት እና ኢንዱስትሪ ልማት መምሪያዎች /ጽ/ቤቶች እንዲሰጡ ይደረጋል፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ልዩ ወረዳዎች ከዚህ ቀደም ፈቃድ የመስጠት ሥራ ያልሰሩ በመሆኑ እና የሰው ኃይል ባለማሟላታቸው የአሠራር ክፍተት እንዳይከሰት ክልሉን እያማከሩ በመናበብ ይሰራሉ፡፡
2. ኢንቨስትመንት ፈቃድ ሰርተፍኬት ማሳተም፣ ማዘጋጀትና ማሰራጨት ሥልጣን የክልሉ ኢንቨስትመንትና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ ይሆናል፡፡
3. በፌደራል ኢንቨስትመንት ኮሚሽን የሚሰጡ ፈቃዶች በክልል ቢሮና ፕሮጀክቱ በሚሰማራበት ኢንቨስትመንት መዋቅር መመዝገብ አለበት፡፡

22. የኢንቨስትመንት ፈቃድ መስጠት

በዞንና ልዩ ወረዳ መዋቅር ደረጃ የሚሰጥ ሆኖ በሚከተለው አግባብ መስተናገድ አለበት፡፡

1. በዞንና ልዩ ወረዳ የሚሰጡ ፈቃዶች በክልሉ ካቢኔ መሬት እንዲያገኙ የውሳኔ ደብዳቤ ያላቸው ፕሮጀክቶች መሆን አለባቸው፡፡
2. በገጠርና በከተማ በግል ይዞታ ላይ የሚከናወኑ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች የኢንቨስትመንት ደረጃ የሚያሟሉና የመሬት ባለቤትነት ሕጋዊነት የተረጋገጠ ከሆኑ በዞንና በልዩ ወረዳ ውሳኔ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ይሰጣል፡፡
3. በሁሉም መዋቅሮች የኢንቨስትመንት ፈቃድ የተሰጣቸው ፕሮጀክቶች በክልሉ መረጃ ቋት መመዝገብ አለባቸው ካልተመዘገቡ ተቀባይነት አይኖራቸውም፡፡

23. ቅጣትን በተመለከተ፡-

አንድ ፈቃድ በዚህ መመሪያ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ያልታደሰ ከሆነ የእድሳት ጊዜው ከተጠናቀቀ 1 (አንድ) ወር ጊዜ በኋላ ባሉት እያንዳንዱ ወር ተጨማሪ ብር 500 (አምስት መቶ) ተጨምሮ የአገልግሎት ክፍያ እንዲከፈል ይደረጋል።

24. አቤቱታና ቅሬታ ስለማቅረብ

1. አቤቱታና ቅሬታ አቀራረብን በተመለከተ የኢንቨስትመንት ፈቃድ በመሰረዙ ወይም በመታገዱ በዞን/ልዩ ወረዳ ኢንቨስትመንት መምሪያ /ጽ/ ቤት ውሳኔ ቅር የተሰኘ ባለሀብት ለቢሮው ቅሬታውን ማቅረብ ይችላል።
2. በቢሮው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ባለሀብት ደግሞ ቅሬታውን ለርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት ማቅረብ ይችላል። በርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት የተሰጠ ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል። ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ውሳኔ ከተሰጠ ከ 6 (ስድስት) ወራት በኋላ የሚቀርቡ ቅሬታዎች ግን በየትኛውም የአስተዳደር እርከን ተቀባይነት አይኖራቸውም።

25. ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረኑ ማናቸውም መመሪያ ወይም የአሠራር ልምድ በዚህ መመሪያ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

26. መመሪያ ስለማሻሻል

ቢሮው አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ይህንን መመሪያ ሊያሻሽል ይችላል።

27. መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በቢሮው ማናጅመንት ጸድቆ በክልሉ ፍትህ ቢሮ ከተመዘገበበት ከ ሰኔ 30/ 2018 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ቡታጅራ

ሰኔ /2018 ዓ.ም

አባስ መሐመድ (ዶ/ር)

የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት

ኢንቨስትመንትና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ ኃላፊ